# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ

መጋቢት 2007

አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግቢያ ..... II

1. አጭር ርዕስ ..... 1
2. ትርጓሜ ..... 1
3. ዓላማ ..... 3
4. የተፈጻሚነት ወሰን እና የሀላፊነት ክፍፍል ..... 4
5. አጠቃላይ ክልከላ ..... 4
6. ስለ ልዩ ፈቃድ ..... 4
7. ልዩ ፈቃድን ስለማደስ እና ለውጥ ..... 5
8. የውጭ ማሸጊያ፣ ገላጭ ጽሁፍ መስፈርቶች እና ስለ ጤና ማስጠንቀቂያ ..... 5
9. የትምባሆ ምርት ይዘት እና ተያያዥ መረጃን ይፋ ማዉጣት ስለማስፈለጉ ..... 7
10. ክልከላ ..... 7
11. ናሙና ስለመሰብሰብ እና መፈተሽ ..... 8
12. አጠቃላይ ክልከላ ..... 8
13. ስለተፈቀዱ መረጃዎች ..... 10
14. ማጨስ የተከለከለባቸው ቦታዎች ..... 11
15. ትምባሆን ለማጨስ ስለተከለለ ክፍል እና ቦታ ..... 13
16. የማስከበር ግዴታ ..... 14
17. ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ከትምባሆ ምርት ስለመጠበቅ ..... 14
18. ሲጋራን በነጠላ ስለ መሸጥ ..... 15
19. አስተዳደራዊ እርምጃዎች ..... 15
20. በወንጀል ተጠያቂ ስለማድረግ ..... 16
21. ህገ-ወጥ የትምባሆ ምርት ንግድ ..... 16
22. የመተባበር ግዴታ ..... 17
23. ስለ ንግድ ሰንሰለት ..... 17
24. ስለ ትምባሆ ምርት አወጋገድ ..... 17
25. የአገልግሎት ክፍያ ..... 17
26. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች ..... 18
27. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ..... 18

## መግቢያ

የትምባሆ ምርቶች የጤና፣የማህበራዊ፣የኢኮኖሚ እና አካባቢያዊ ችግር የሚያስከትሉ በመሆናቸው፤

ትምባሆን መጠቀም እንደ ካንሰር፣ የመተንፈሻ አካል ህመም፣ የልብ እና የደም ስር የመሳሰሉትን በሽታዎች፣ የአካል ጉዳትን እንዲሁም ሞትን እንደሚያስከትል በሳይንስ የተረጋገጠ በመሆኑ፤

ለትምባሆ ጢስ መጋለጥ ትምባሆ በማያጨሱ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የጤና ችግር፤ ሞት እና የአካል ጉዳት ስለሚያስከትል እና ይህንኑ መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሀገሪቱ ትምባሆን የሚጠቀሙ ወጣቶችና ጎልማሶች ቁጥር እንዳይጨምር፤ የትምባሆ ምርትን ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድርግ ትምባሆ የመጠቀም ፍላጎትን እንዲጨምር የሚያደርግ በመሆኑ እና ይህንን የትምባሆ ሽያጭ መንገድ መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአለም የጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ኮንቬንሽን መሰረት መንግስት የትምባሆ ምርት መጠቀም እና የትምባሆ ጭስ ተጋላጭነትን ከመከላከል እና ለመቀነስ ግዴታ በተጨማሪ የኒኮቲን ንጥረነገር ሱሰኝነት እና ጥገኝነት የመከላከል እና የመቀነስ ሀላፊነት ስላለበት፤

የኒኮቲን ንጥረ ነገር ያለውም ይሁን የሌለው የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን መስጫ መሳሪያ (Electronic Nicotine Delivery System) መጠቀም ለትምባሆ ተጠቃሚዎች ተቀጣጣይ ትምባሆን (combustible tobacco) ከመጠቀም በአንፃራዊ መንገድ ያነሰ ጉዳት እንዳለው ቢገለጽም በአሁኑ ሰአት በሀገራችን የትምባሆ ተጠቃሚነት ስርጭት ዝቅተኛ ስለሆነ እና የህብረተሰብ ጤና በተለይ የማያጨሱ ሰዎች፣ ህጻናትን፣ ነፍሰጡር እናቶች እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍል በአግባቡ ለመጠበቅ ሲባል እና በመተግበር ላይ ያሉ የትምባሆ ቁጥጥር ስራዎችን ዉጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈጸም እንዲቻል ይህንን ምርት በህግ መከልከል አሳማኝ ሆኖ በመገኘቱ፤

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የትምባሆን ቁጥጥር በተመለከተ በአለም የጤና ድርጅት የወጣውን የትምባሆ ቁጥጥር ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 822/2006 ለማስፈጸም አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስድ ስልጣን የሰጠው በመሆኑ፤

በትምባሆ ቁጥጥር ኮንቬንሽኑ ውስጥ ካሉ የትምባሆ ቁጥጥር ስራዎች ውስጥ የተወሰኑ ስራዎችን ለክልል መንግስት መስጠቱ ኮንቬንሽኑን በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚረዳ እና አስፈላጊ እርምጃ ሆኖ በመገኘቱ፤

በትምባሆ ቁጥጥር ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 822/2006 አንቀጽ (4)፣ በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 55(3) እና በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀጽ 98 መሰረት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን ይህን የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 28/2007 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) "የትምባሆ ምርቶች" ማለት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ከትምባሆ ቅጠል የተዘጋጀ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ፣ በማሽተት ወይም በሌላ መንገድ የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ሆኖ የጋያ ወይም የሺሻ ትምባሆን ይጨምራል፤

   2) "የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን መስጫ መሳሪያ" ማለት የኤሌክትሮኒክ ሲጋራን ጨምሮ ኒኮቲን ያለው ወይም የሌለውን ውህድ በማሞቅ ለመጠቀም የሚያገለግል መሳሪያ ነው፤

   3) "ትምባሆን ማስተዋወቅ" ማለት እንደ መገናኛ ብዙሃን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ የቴሌኮምን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅ እና የፋክስ አገልግሎቶችን እና መሰል የሆኑ መንገዶችን በቀጥታ በመጠቀም የትምባሆ ምርቶችን ወይም ትምባሆ መጠቀምን ለማበረታታት ተብሎ ወይም ሊያበረታታ በሚችል ሁኔታ የሚደረግ ማንኛውም አይነት የንግድ ግንኙነት፣ አስተያየት ወይም ተግባር ነው፤

   4) "የትምባሆ ፕሮሞሽን" ማለት የትምባሆ ምርትን በፅሁፍ፣ በድምጽ ወይም በምስልከአንድ ፕሮግራም ጋር በማካተት፤ ለማህበራዊ ፋይዳ የሚውል መዋጮ ወይም ስጦታን በመጠቀም፣ የፕሮሞሽናል ቁሶች ወይም እቃዎችን በመስጠት እና መሰል በሆኑ መንገዶች በመጠቀም የትምባሆ ምርቶችን ወይም ትምባሆ መጠቀምን በተዘዋዋሪ ለማበረታታት ተብሎ ወይም ሊያበረታታ በሚችል ሁኔታ የሚደረግ ማንኛውም አይነት የንግድ ግንኙነት፣ አስተያየት ወይም ተግባር ነው፤

   5) "ትምባሆን ስፖንሰር ማድረግ" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትምባሆ ምርቶችን ወይም ትምባሆ መጠቀምን ለማበረታታት ተብሎ ወይም ሊያበረታታ በሚችል ሁኔታ ለማንኛውም አይነት ዝግጅት፣ ኩነት፣ ወይም ለግለሰብ የሚደረግ ድጋፍ ነው፤

   6) "የጤና ማስጠንቀቂያ" ማለት ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት በውጭ ማሸጊያ ላይ በጽሁፍ ወይም የባለቀለም ምስል ትምባሆ መጠቀም እና ለትምባሆ ጢስ መጋለጥ የሚያስከትለውን የጤና ጉዳት የሚያሳይ ማስጠንቀቂያ ነው፤

7) "ይዘት" ማለት የትምባሆ ቅጠልን ጨምሮ የትምባሆ ግብአት፣ ግብአቱን ለማምረት የሚጠቀሙ ንጥረ ነገሮች፣ ጭማሪዎችን፣ ለዝግጅት የሚያግዙ ነገሮች፣ ትምባሆ ውስጥ የሚገኝ ቅሪት እና ከማሸጊያ ወደ ትምባሆ ምርቱ ሊገባ የሚችል ማንኛውም ነገር ነው፤

8) "ልዩ ፈቃድ" ማለት የትምባሆ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ በጅምላ ለመሸጥ፣ ለማከፋፈል ወይም ለመቸርቸር አግባብ ባለው የጤና ተቆጣጣሪ አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

9) "ጅምላ ሻጭ" ማለት የትምባሆ ምርትን ከአንድ ክልል በላይ በማከፋፈል ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

10)"የትምባሆ ቸርቻሪ" ማለት የትምባሆ ምርቶችን ብቻ በመያዝ ትምባሆን በችርቻሮ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤

11)"ሁለተኛ ደረጃ የትምባሆ ጭስ" ማለት ከሚቀጣጠል ሲጋራ ወይም የትምባሆ ምርት የሚለቀቅ ጢስ ሆኖ በአብዛኛው አጫሹ በትንፋሹ ከሚለቀው አየር ጋር ተቀላቅሎ የሚወጣ ነው፤

12)"ማጨስ" ማለት የትምባሆ ጢስ በትንፋሽ ወደ ሰውነት ውስጥ እየተሳበ ወይም በትንፋሽ ወደ ውጭ የሚለቀቅ ሆኖ የተለኮሰ የትምባሆ ምርት መያዝንም ይጨምራል፤

13)"የውጭ ማሸጊያ" ማለት የትንባሆ ምርት በችርቻሮ የሚቀርብበት ማንኛውም ማሸጊያ ነው፤

14) "ገላጭ ጽሁፍ" ማለት ስለ ትንባሆ ምርት አስፈላጊውን መረጃ የሚገልጽ በማሸጊያው ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ጽሁፍ ነው፤

15)"ለህዝብ ክፍት የሆኑ ቦታዎች" ማለት ለህዝብ ክፍት የሆነ ወይም የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሰው ሊገባበት የሚችል ማንኛውም ስፍራ ነው፤

16)"ከበር መልስ ያለ ቦታ (indoor place)" ማለት የተሰራበት ቁሳቁስ አይነት እና መዋቅሩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ መሆኑ ሳይወስነው ማንኛውም በጣሪያ የተሸፈነ እና አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ግድግዳ የተከለለ ስፍራ ነው፤

17)"የስራ ቦታ" ማለት በክፍያም ይሁን ካለ ክፍያ አንድ ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች የስራ ሀላፊነታቸውን የሚያከናውኑበት ስፍራ ሲሆን እነዚህ ሰዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚጠቀሙበት የጋራ ስፍራን ይጨምራል፤

18)"ክፍት ቦታ" ወይም "ከበር ዉጭ ያለ ቦታ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ያልተከለለ ቦታ ነው፤

19)“ለማጨስ የተለየ ክፍል ወይም ቦታ” ማለት ትምባሆን ለማጨስ በተከለከሉ ቦታዎች ውስጥ ለሚያጨሱ ሰዎች ተብሎ የዚህን መመሪያ መስፈርቶች በሚያሟላ መልኩ የተከለለ ክፍል ወይም ቦታ ነው፤

20)“የህዝብ ማጓጓዣ” ማለት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር ሰዎችን በክፍያ ለማጓጓዝ የሚያገለግል ማንኛዉም የመጓጓዣ አይነት ሆኖ ሰርቪስንም ይጨምራል፤

21)“ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

22)“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራለዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ላይ የተዘረዘሩት ክልሎች ሲሆኑ አዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አሰተዳደርን ይጨምራል፤

23)“የከተማ አስተዳደር” ማለት በሕግ ወይም በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፤

24)“አግባብ ያለው አካል” ማለት የጤና፣ የንግድ፣ የትምህርት፣ የትራንስፖርት፣ የባህል እና ቱሪዝም፣ የገቢ እና ጉምሩክ ወይም የማስታወቂያ ስራ የሚሰራን ጨምሮ በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግበትን ጉዳይ ለማስፈጸም በፌደራል እና በክልል ደረጃ ሀላፊነት ያለበት ሌላ አግባብ ያለው የመንግስት አካል ነው፤

25)“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰውን እና በህግ የሰው መብትን የተሰጠው አካልን ይጨምራል፤

26) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ትምባሆን በመጠቀምና በትምባሆ ጢስ መጋለጥ ምክንያት በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰውን የጤና፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጉዳቶች ለመከላከል፤ እና ኢትዮጵያ በአለም የጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ኮንቬንሽን፣ የኮንቬንሽኑ ማስፈጸሚያ ጋይድላይኖች፣ እና አግባብ ባላቸው የትምባሆ ቁጥጥር ኮንቬንሽን ፕሮቶኮሎች ውስጥ የገባችውን ግዴታዎች እንደአግባቡ ለማስፈጸም ነው፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን እና የሀላፊነት ክፍፍል

1) ይህ መመሪያ ወደሀገር ውስጥ በሚገባ፣ በሚከፋፈል፣ እና በሚሸጥ ማንኛውም የትምባሆ ምርት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) በመመሪያው ክፍል 2 እና 3 መሠረት ለትምባሆ አስመጪ እና ጅምላ ሻጭ የሚሰጥን ልዩ ፈቃድ፣ የውጭ ማሸጊያ፣ ገላጭ ጽሁፍ፣ የምርት ይዘት፣ የጤና ማስጠንቀቂያ፣ ናሙና ስለመሰብሰብ እና መፈተሽ፣ የትምባሆ ማስተዋወቅና ፕሮሞት ማድረግ፣ ትምባሆ ስፖንሰር ማድረግ የሚመለከቱ የቁጥጥር ሀላፊነቶችን ባለስልጣኑ ያስፈጽማል፡፡

3) በአንድ ክልል የተወሰነ የትምባሆ ምርትን ማከፋፈል፣ ሽያጭ፣ የትምባሆ ማስተዋወቅና ፕሮሞት ማድረግ፣ ትምባሆ ስፖንሰር ማድረግ እንዲሁም የዚህን መመሪያ ክፍል 4 በተመለከተ አግባብ ያለው የክልል አካል ያስፈጽማል፡፡

5. አጠቃላይ ክልከላ

የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን መስጫ መሳሪያ ማምረት፣ ወደሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም በማንኛውም መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የልዩ ፈቃድ መስፈርቶች

6. ስለ ልዩ ፈቃድ

1) ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳይሰጠው የትምባሆ ምርትን ለንግድ ተግባር ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከፋፈል ወይም በጅምላ መሸጥ አይችልም፡፡

2) በአንድ ክልል ውስጥ የተወሰነ የትምባሆ ምርት ጅምላ መሸጥን፣ ማከፋፈልን ወይም ችርቻሮን በተመለከተ የልዩ ፈቃድ አሰጣጥ እና አሰራር አግባብ ያለው የክልል መንግስት አካል በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት ይሆናል፡፡

7. ልዩ ፈቃድን ስለማደስ እና ለውጥ

1) በአንቀፅ 6 መሰረት የተሰጠ ልዩ ፈቃድ የሚፅናው ለአንድ አመት ሆኖ፤ ይኸውም በኢትዮጵያ የበጀት አመት የመጀመሪያው ወር ላይ (ከሀምሌ1-ሀምሌ 30) መታደስ አለበት፡፡

2) በአንቀፅ 6 መሰረት የተሰጠ ልዩ ፈቃድ በበጀት አመቱ መግቢያ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካልታደሰ በየወሩ100% በተጨማሪ የልዩ ፈቃድ ክፍያ በማድረግ በሚቀጥሉት ሁለት ተከታታይ ወሮች ውስጥ ማሳደስ ይቻላል፡፡

3) በኢትዮጵያ የበጀት አመት መግቢያ ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራቶች ጊዜ ውስጥ ፈቃዱ ካልታደሰ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ከዚህም በኃላ የሚደረግ ማንኛውም የትምባሆ የንግድ እንቅስቃሴ ከልዩ ፈቃድ ውጪ እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

4) አስመጪዎች እና ጅምላ አከፋፋዮች መጀመሪያ ከተሰጣቸው ልዩ ፈቃድ የተለየ አዲስ የሆነ የትምባሆ ምርት ለመሸጥ ሲፈልጉ ፈቃዱ መለወጥ አለበት፡፡

8. የውጭ ማሸጊያ፣ ገላጭ ጽሁፍ መስፈርቶች እና ስለ ጤና ማስጠንቀቂያ

1) በትንባሆ ምርት የውጭ ማሸጊያ እና ገላጭ ጽሁፍ ላይ የምርቱን ባህሪ፣ ጤና ላይ የሚኖረውን ውጤት፣ ጉዳት፣ ወይም ልቀቱን በሚመለከት የተሳሳተ አረዳድ የሚፈጥር አገላለጽ ጨምሮ ሌላ ምልክት ማድረግ የተከለከለ ሆኖ አንድ የትንባሆ ምርት ከሌላ የትንባሆ ምርት ያነሰ ጉዳት እንዳለው በማንኛውም መንገድ መግለጽ የተከለከለ ነው፡፡

2) በትንባሆ ምርት ላይ አነስተኛ ታር (low tar)፣ ቀላል (light)፣ በጣም ቀላል (ultralight)፣ ማይልድ (mild)፣ ኤክስትራ (extra)፣ አልትራ (ultra) እና ተመሳሳይ አገላለጾችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

3) የትምባሆ ልቀትን በቁጥር ወይም በሌላ መግለጫ የትንባሆ ምርቱ ላይ፣ የውጭ ማሸጊያው ላይ ወይም በማንኛውም የትንባሆ ምርት ውስጥ መግለጽ ተከለከለ ነው፡፡

4) የትምባሆ ምርቶችን ያገልግሎት ጊዜያቸው መቼ እንደሚያበቃ በውጭ ማሸጊያውም ሆነ በገላጭ ጽሁፉ ላይ መግለፅ የተከለከለ ነው፡፡

5) ማንኛውም የትምባሆ ምርት የውጭ ማሸጊያ እና ገላጭ ጽሁፍ የጤና ማስጠንቀቂያ መያዝ አለበት፡፡ የጤና ማስጠንቀቂያው የማሸጊያውን የፊት እና ጀርባ ገጽ ለየብቻው ከ30% ያላነሰ ቦታ የሸፈነ መሆን አለበት፡፡

6) የትምባሆው የውጭ ማሸጊያው አሰራር ምርቱ በመደበኛ መልኩ በሚከፈትበት ጊዜ የትኛውንም የጤና ማስጠንቀቂያ መልዕክት ላይ ጉዳት በሚያደርስ፣ በሚከልል፣ በሚያጨልም ወይም እንዳይታይ በሚሸፍን ሁኔታ መሆን የለበትም፡፡

7) የጤና ማስጠንቀቂያዉ ሌሎች አስፈላጊ በሆኑ የማሸጊያ ወይም ገላጭ ጽሁፍ መስፈርቶች ወይም አምራቹ፣ አስመጪው፣ ጅምላ አከፋፋይ ወይም ሌላ ማንኛውም የትምባሆ ነጋዴ በማሸጊያው ላይ በሚያስቀምጠው ሌላ ማንኛውም ነገር መሸፈን ወይም መከለል የለበትም፡፡

8) በውጭ ማሸጊያ ላይ የሚገለጽ የጤና ማስጠንቀቂያ ጉልህ፣ ግልፅ፣ የሚታይ እና በቀላሉ የሚነበብ እና በቀላሉ የማይለቅ ሆኖ በማሸጊያው የላይኛው የፊት እና ጀርባ ገጽ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

9) በውጭ ማሸጊያ ላይ የሚቀመጥ የጤና ማስጠንቀቂያ መቀመጥ ያለበት ማስጠንቀቂያውን በጉልህ ሊያሳይ በሚያስችል ሁለት ተቃራኒ ቀለማት መሆን አለበት፡፡

10) የትምባሆ ምርቶች የውጭ ማሸጊያ የንግድ ስም፣ የምርቱ ስም፣ የአምራቹን ስም እና አድራሻ፣ የአምራቹን ሀገር፣ በፓኬት ውስጥ ያለውን የምርቱን ብዛት እና ሌላ በባለስልጣኑ ከሚፈቀድ ነገር ውጭ ሌላ መረጃ መያዝ የለበትም፡፡

11) የጤና ማስጠንቀቂያ ጽሁፍ በአማርኛ ወይም በእንግዘኛ ቋንቋ መጻፍ አለበት፡፡

12) ባለስልጣኑ የጤና ማስጠንቀቂያን የጊዜ ቀመር በማዘጋጀት ማስጠንቀቂያው የሚቀየርበትን አኳኋን በተመለከተ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

13) ባለስልጣኑ ትምባሆ ማጨስ ሱስ ያሲዛል፣ አደገኛ የሳንባ በሽታ፣ ካንሰር፣ ብሮንካይት፣ የልብ በሽታን ያመጣል፣ ፅንስን ይጎዳል፣ ልጅዎን ይጎዳል፣ በአካባቢዎ ያሉትን በማያጨሱ ሰዎች ላይ የጤና መቃወስ ያመጣል፣ ካለ እድሜ ይገድላል ወይም ማጨስ ቢያቆሙ በከፍተኛ ሁኔታ ጤናዎን የሚያውኩ ስጋቶችን መቀነስ ይችላሉ የሚሉ

ገለፃዎችን ጨምሮ ሌሎች የጤና ማስጠንቀቂያዎች በውጭ ማሸጊያ ላይ እንዲገቡ ያዛል፡፡

14)ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚያስቀምጣቸው የጤና ማስጠንቀቂያዎች ከ12 ወራት ለማይበልጥ ጊዜ ሲያገለግሉ ለሚቀጥለው ጊዜ በሌሎች የጤና ማስጠንቀቂያዎች እንዲቀየሩ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ባለስልጣኑ ይህንን አንቀጽ ለማስፈጸም ቁጥጥር ለሚደረግበት ሰው ከሶስት ወራት በፊት በደብዳቤ ያስታውቃል፡፡

15)የጤና ማስጠንቀቂያዎች በእያንዳንዱ ብራንድ ግንድ (brand family) ወይም በአንድ ብራንድ ግንድ ውስጥ ላሉ ምርቶች (each variant within the brand family) ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው መሰረት በውጭ ማሸጊያ ላይ በእኩል ቁጥር መቀመጥ አለበት፡፡

16)በህግ ከተፈቀደው ዉጭ የተለየ ማሸጊያ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

## 9. የትምባሆ ምርት ይዘት እና ተያያዥ መረጃን ይፋ ማዉጣት ስለማስፈለጉ

1) የትምባሆ ምርትን ለማምረት የዋሉ ይዘቶች ለውጥ ከተደረገባቸው አምራቹ ወይም አስመጪው ባለስልጣኑ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

2) ባለስልጣኑ አምራቾች እና አስመጪዎች ስለ ንግድ ድርጅቱ አጠቃላይ መረጃ፣ በትምባሆ ምርቱን ወይም ልቀትን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ፤ የሽያጭ መረጃ እና የምርቱን ውህድ፣ ይዘቶች፣ ጎጂ ባህሪያቶችን እና የተለዩ ቅንጣቶች (brand elements) ጨምሮ ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ሊያዝ ይችላል፡፡

## 10.ክልከላ

1) ማንኛውም ሰው ተጨማሪ ጣዕም ያለው የትምባሆ ምርት (flavored tobacco product) ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም ለመሸጥ ማቅረብ አይችልም፡፡

2) ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርት ይዘቶች ለጤና የሚጠቅም ወይም ጤና ላይ የሚያስከትልን ጉዳት የሚቀንስ የማስመሰል ውጤት የሚፈጥሩ እንደ ቫይታሚን፣ ፍራፍሬ እና አትክልቶች፣ አሚኖ አሲድ፣ጠቃሚ ፋቲ አሲዶች እና ሀይልን እና

ጥንካሬን ከመስጠት ጋር የተያያዙ አነቃቂ ውህዶችን የያዘ የትምባሆ ምርት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም ለመሸጥ ማቅረብ አይችልም።

3) "ተጨማሪ ጣዕም ያለው የትምባሆ ምርት" ማለት ለብቻው ወይም ከሌላ የትምባሆ ይዘት ጋር አንድ ላይ ሆኖ ትምባሆው ሳይቀጣጠል ወይም ትምባሆው በሚቀጣጠልበት ጊዜ ከትምባሆ ጣእም ወይም ቃና ውጭ ያሉ እንደ ፍራፍሬ፣ ቸኮሌት፣ ቫኒላ፣ ማር፣ ከረሜላ፣ ካካዎ፣ ሜንቶል፣ ሚንት፣ የአልኮል መጠጥ፣ እጽዋት (herbs) ወይም ቅመም (spice) የመሳሰሉ የተለየ (distinguishable) ጣእም ወይም ቃና የሚሰጥ ይዘት ያለው ማንኛውም የትምባሆ ምርት ነው።

## 11. ናሙና ስለመሰብሰብ እና መፈተሽ

1) ባለስልጣኑ ከማምረቻ ቦታዎች፣ ቁጥጥር በሚያደርግበት የመግቢያ ኬላዎች፣ ልዩ ፈቃድ ለመስጠት ወይም በኢንስፔክሽን ወቅት ናሙና መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ማንኛውም ጊዜ የትምባሆ ምርቶችን ናሙና መውሰድ ይችላል። በዚህ ንኡስ አንቀጽ የሚወሰድ ናሙና ለምርመራ ወይም ለፍተሻ ተግባር ብቻ የሚውል ይሆናል።

2) ባለስልጣኑ የትምባሆ ምርቱን በተመለከተ ዕውቅና ካለው ላብራቶሪ እንዲፈተሽ ሊያደርግ ይችላል። በዚህ መሰረት ለሚደረግ የላብራቶሪ ፍተሻ ባለስልጣኑ የምርቱን ባለቤት የፍተሻ ወጭ ሊጠይቅ ይችላል።

# ክፍል ሦስት

# ትምባሆን ማስተዋወቅ፣ፕሮሞሽን እና ስፖንሰር ማድረግ

## 12. አጠቃላይ ክልከላ

1) የትምባሆ ምርትን ማስተዋወቅ፣ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድረግ የተከለከለ ነው።

2) የትምባሆ ምርት በተመለከተ ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድረግ ፍፁም የተከለከለ መሆኑ በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

ሀ) በድምፅ፣ በምስል ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የግንኙነት መንገዶች፣ በህትመት፣ በፊልሞች፣ በዲቪዲ፣ በቪዲዮ እና በሲዲ መጫወቻዎች ወይም ሌሎች የዲጅታል

መገናኛዎች፣ቲያትር ወይም የቀጥታ ስርጭቶች አማካኝነት ትምባሆን የሚመለከት ኮሚኒኬሽን ማድረግ፤

ለ) የትምባሆ ምርቶቹን ለመሸጥ የሚደረጉ ስጦታዎች እና ትምባሆን ሲሸጡ እንደ ቁልፍ መያዣ፣ ቲሸርቶች፣ ኮፍያዎች እና የሲጋራ መለኮሻዎች የመሰሉ እቃዎች መስጠት ወይም በማንኛውም መንገድ መሰል ማበረታቻ ማድረግ፤

ሐ) የገበያ ጥናት እና የጣዕም ቅምሻን ጨምሮ መሰል ነገሮች በማድረግ የትምባሆ ምርቶችን ነፃ ናሙና ማቅረብ፤

መ) የዋጋ ቅናሽ መልእክትን ያዘለ በማንኛውም መንገድ የሚደረግ ማስተዋወቅ፣

ሠ) የማበረታቻ ፕሮሞሽን እና የትምባሆ ምርቶችን ግዢ ለሚፈጽም ማንኛውም ሰው ሌሎች እቃዎችን የሚገዛበትን ነፃ ኩፖን መስጠትን ጨምሮ ሌሎች ተመሳሳይ የምርቃት (loyality schemes) አይነት ተግባሮችን መፈፀም፤

ረ) የትምባሆ ምርት የብራንድ ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት፣ የድርጅት አርማ፣ የንግድ መለያ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መለያን የትምባሆ ምርት ካልሆኑ ሌሎች ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ጋር ማያያዝ (brand stretching) ወይም ትምባሆ ነክ ያልሆኑ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በተመሳሳይ መንገድ ከትምባሆ ምርት ጋር ቁርኝነት ወይም ተያያዥነት እንዳላቸው (brand sharing) ማሳየት፤

ሰ) መረጃን ጨምሮ ቀጥታ ግለሰቦች ላይ በማነጣጠር ቀጥታ መልዕክት ወይም ደብዳቤ መላክ፣ በስልክ መገበያየት፣የሸማቾች ቅኝት ወይም ጥናት ማካሄድን እና ተመሳሳይ አይነት የፕሮሞሽን መንገዶች መጠቀም፤

ሸ) የትምባሆ ምርት ነጋዴ የተወሰነ የትምባሆ መጠን ያለውን ምርት ሲሸጥ ሽልማት መስጠትን ጨምሮ ሌሎች የማበረታቻ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም ሽያጭን ማበረታታት ጨምሮ ለትምባሆ ሻጭ የሚደረግ ተያያዥ ክፍያ ወይም ሌላ አይነት ድጋፍ ማድረግ፤

ቀ) በትምህርት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ የመስተንግዶ (hospitality) ቦታዎች፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ በመዝናኛ ቦታዎች፤ በሙዚቃ እና ዳንስ ቤቶች

እና የማህበራዊ ቦታዎች ወይም ዝግጅቶች ላይ የትምባሆ ምርቶችን መሸጥ፣ማቅረብ፣ ማስቀመጥ እና በግልፅ ማሳየት፤ እና

በ) አሻንጉሊቶችን፣ ጣፍጭ ምርቶችን ወይም ሌሎች ምርቶችን የትምባሆ ምርት በማስመሰል ማምረት፣ ወደሀገር ውስጥ ማስገባት፣ መሸጥ ወይም ማቅረብ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (2) መሰረት የትምባሆ ምርትን በማስተዋወቅ፣ፕሮሞት እና ስፖንሰር በማድረግ በማንኛውም መንገድ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው መረጃውን በሚቆጣጠርበት ሁኔታ ላይ ካለ የተከለከለውን ስርጭት የማስነሳት ወይም እንደ አግባቡ መረጃው ወይም ስርጭቱ ተደራሽ እንዳይሆን ሌላ ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

13.ስለተፈቀዱ መረጃዎች

ምንም እንኳን የትንባሆ ምርትን ሳይታሰብ ፕሮሞት ሊያደርጉ ቢችሉም የሚከተሉት መረጃዎች የተከለከሉ አይደሉም፡-

1) የትንባሆ ምርት ብራንድ ስም፣ የእሽግ መጠን፣ ዋጋ ወይም በህግ እንዲገለጽ የሚደረግ ሌላ መረጃ በስተቀር የትንባሆ ምርት ዋጋ ዝርዝርን ሌላ መረጃ ሳይዝ የትንባሆ ምርት ህጋዊ በሆነ መንገድ በሚሸጥበት ቦታ በጥቁር እና ነጭ ቀለም የተጻፈ የዋጋ ዝርዝር መለጠፍ ወይም ማስቀመጥ፤

2) አግባብ ባለው ህግ በተደነገገ መስፈርት፣ ክልከላ እና ወሰን መሰረት የትንባሆ ምርት ብራንድ ስም፣ ምርት ስም የአምራች ስምን እና ሌላ የሚፈቀድ መረጃን በትንባሆ ምርት ላይ ማሳየት፤

3) በትንባሆ አምራች፣ ሻጭ ወይም እነዚህን በሚወክል ሌላ ሰው የተደረገ ምንም አይነት የገንዘብ ወይም የአይነት ክፍያ ከሌላ በመገናኛ ብዙሀን ላይ የትምባሆ ምርትን ወይም መጠቀምን በተመለከተ በአጋጣሚ፣ ወይም በታሪካዊ እውነታ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጋዜጠኝነት ወይም የአርቲስት ስራ ላይ ወይም ትምህርታዊ ለሆነ አላማ የሚደረግ ገለጻ፤ እንደዚህ አይነት የጋዜጠኝነት ወይም የአርቲስት ስራ ገለጻ ሲደረግ ትምባሆ መጠቀም ጤናን እንደሚጎዳ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መልእክት ከፕሮግራሙ በፊት መገለጽ አለበት፤

4) በትንባሆ አምራች፣ ሻጭ ወይም እነዚህን በሚወክል ሌላ ሰው የተደረገ ምንም አይነት የገንዘብ ወይም የአይነት ክፍያ ከሌላ የትምባሆ ምርትን ወይም መጠቀም በሚመለከት እውነተኛ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ወይም ሳይናሳዊ አስተያየት፤

5) መረጃው ለንግድ ስራ አስተዳደር ወይም የኮርፖሬሽን ሪፖርት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና  የአካባቢ ጥበቃ ወይም መልካም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮችን ጨምሮ ሌላ ማህበራዊ ፋይዳ ያለው ስራን በሚመለከት በትንባሆ ድርጅትን የሚሰራጭ መረጃ ወይም ሪፖርት፤

6) መረጃው የሚሰጠው ለነጋዴው ብቻ የተወሰነ ከሆነ የትንባሆ ምርትን በሚመለከት ለንግድ ውሳኔ ሊረዳ ወይም ሊጠቅም የሚያስችል መረጃ ለትንባሆ ነጋዴ መስጠት፤ እና

7) መረጃው የሚሰጠው ለዚሁ ብቻ የተወሰነ ከሆነ የትንባሆ አምራች ለሰራተኞቹ፣ ኮንትክተር፣ የግብአት አቅራቢዎች፣ እና ከምርቱ ንግድ ጋር አጋር ለሆኑ ድርጅቶች (business partners) የሚዘጋጀው የመረጃ ወረቀት (newsletters)፡፡ በአምራቹ፣አስመጪው ወይም የጅምላ ሻጩ እና በገዢዎቻቸው፣ንግድ አጋሮች፣ሰራተኞች ወይም ሸሪኮች መካከል በሚኖር የንግድ ግንኙነት ስለ ትምባሆ ምርቱ፣ ስለ ባህሪው፣ ስለ መገኛ ቦታው እና ዋጋው፣ ስለ ምርቱ ምስል፣ ምርቱ ስለተሰራበት አካል እና ስለ አስተሻሸጉ ትክክለኛውን ወይም እውነተኛውን መረጃ ከማስታወቅ በስተቀር ማንኛውንም አይነት መረጃ መግለፅ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ለትምባሆ ጭስ ስለመጋለጥ እና ስለ ትምባሆ ምርት ሽያጭ

### 14. ማጨስ የተከለከለባቸው ቦታዎች

1) ለህዝብ ክፍት በሆኑ ከበር መልስ ያሉ ቦታዎች፣ ከበር መልስ ያለ የስራ ቦታ፣ እና በህዝብ መጓጓዣዎች  ውስጥ ማጨስ የተከለከለ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተገለፀው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ከበር መልስ ያሉ የስራ እና ለህዝብ ክፍት የሆኑ ቦታዎች ማጨስ የተከለከለ ነው፡፡

ሀ) በጤና ተቋማት እና በትምህርት ተቋማት፤

ለ) በምግብ ቤቶች፣ በሆቴሎች ወይም በሌላ የመመገቢያ ቤቶች፣ በመጠጥ ቤቶች፣ በምሽት ክለብ፣ በካፌዎች፣ በመዝናኛ ክበብ፣

ሐ) ማረሚያ ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያ እና በየትኛውም አይነት የመንግስት መስሪያ ቤቶች፤

መ) በመስሪያ ቤት ኮሪደሮች፣ እንግዳ መቀበያ ቦታዎች፣ በሊፍት እና ደረጃዎች ላይ፣ በመጸዳጃ እና መታጠቢያ ቦታዎች፤

ሠ) በፋብሪካዎች እና የንግድ መደብሮች፤

ረ) ሲኒማ፣ ቲያትር እና ቪዲዮ ቤቶች፣ የሙዚቃ ማሳያ አዳራሾች፣ የህዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾች እና ሌሎች ትዕይንት የሚደረግባቸው ቦታዎች፤

ሰ) የመስህብ ቦታዎች እና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፤እና

ሸ) ባቡር ጣቢያ፣ አውሮፕላን ጣቢያ እና አውቶቢስ ጣቢያ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) በተጠቀሰው መሰረት ከበር መልስ ያልሆነ ስፍራ ቢሆንም ለህፃናት ወይም ዕድሜያቸው ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆች አገልግሎትን በሚሰጡ እንደ ህፃናት መጫወቻ ስፍራ፣ መዋለ ህጻናት፣ የትምህርት ተቋማት፣ ማንኛውም ህፃናት የሚሰበሰቡበት ቦታ እና ወጣት ማዕከላት በመሳሰሉት ቅጥር ግቢ ውስጥ ማጨስ የተከለከለ ነው፡፡

4) ማንኛውም ሠው በህዝብ ማጓጓዣ አውቶብስ፣ ታክሲ፣ ባቡር፣ አየር መጓጓዣ፣ አምቡላንስ ወይም በማንኛውም ህዝብን ለማጓጓዝ የሚያገለግል መጓጓዣ ውስጥ ማጨስ የተከለከለ ነው፡፡

15. ትምባሆን ለማጨስ ስለተከለለ ክፍል እና ቦታ

1) በዋናነት ህፃናት ወይም ዕድሜያቸው ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆች አገልግሎት በሚሰጡ ቦታዎች፣ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ከትምህርት እና ጤና ተቋም ክፍሎች በስተቀር በህግ እንዳይጨስበት የተከለከለ ቦታ ውስጥ ማጨስ የሚፈቀደው ማጨስ የተከለከለበት ለህዝብ ክፍት የሆነ ቦታ ወይም የስራ ቦታ ባለቤት ለዚህ አላማ ተብሎ የከለለው ወይም የሰየመው ልዩ ክፍል ካለ በዚህ ክፍል ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሰረት ለማጨስ የተከለለ ወይም የተሰየመ ክፍል ለብቻው የአየር ማናፈሻ (ventilation) የተገጠመለት ሆኖ፤

   ሀ) የአየር ማናፈሻው በማጨሻ ክፍሉ ውስጥ የሚኖር አየር በድጋሚ ተዘዋውሮ እንዳይገባ ወይም ጭሱ በሌላ መንገድ እንዳይጨስ ወደተከለከለበት ቦታ እንዳይሰራጭ ወይም እንዳይገባ ለመቀነስ አየርን በቀጥታ ወደውጭ ማስወጣት የሚያስችል፤

   ለ) የማጨሻ ክፍሉ በአየር ማናፈሻ (ventilation) መሳሪያ በኩል ካልሆነ በስተቀር ከወለሉ ጀምሮ እስከ ኮርኒሱ ወይም ጣሪያው ድረስ ጭሱ እንዳይወጣ በሚያስችል ሁኔታ በአግባቡ የተሰራ እና የሚዘጋ በር ያለው፤ እና

   ሐ) የማጨሻ ክፍሉ የማያጨሱ ሰዎች ለማንኛውም አገልግሎት ወይም አላማ እንዲያልፉበት፣ እንዲዘዋወሩበት ወይም በየትኛውም መልኩ እንዲገቡበት በሚያደርግ ሁኔታ ያልተሰራ

   መሆን አለበት፡፡

3) በዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ ወይም በሌላ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ወይም በህዝብ ትራንስፖርት ጣቢያ ግቢ ውስጥ ማጨስ የሚፈቀደው ለዚህ አላማ ተብሎ በተከለለ ልዩ ቦታ ብቻ ነው፡፡

4) ትምባሆ ለሚያጨሱ ተገልጋዮች ተብሎ ካልሆነ በስተቀር በዋናነትየትምባሆ ምርትን ለማስጨስ ታስቦ የተከለለ ክፍል ማቋቋም የተከለከለ ነው፡፡

16.የማስከበር ግዴታ

1) ለህዝብ ክፍት የሆነ  ቦታ ወይም ማጓጓዣ ባለንብረት ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ሰው ወይም የስራ ቦታን በተመለከተ አሰሪ ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርት በማይጨስበት ቦታ ላይ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የማስከበር እና እንዳይጣስ የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ አለበት

ሀ) ማጨስ በሕግ ያለመፈቀዱን የሚገልጽ ምልክት በመግቢያና በሌላ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ላይ መለጠፍ፤

ለ) ደንቦች በአግባቡ እየተተገበሩ መሆናቸውን መከታተል፤

ሐ) ሰዎች እንዳያጨሱ መከልከል፣ ፈጽመው የተገኙ እንደሆነ አካባቢውን ወይም የሕዝብ መጓጓዣውን ለቀው እንዲወጡ ማድረግ፣ አግባብ ከሆነ አገልግሎቱን ማቋረጥ እና ለህግ አካል ማሳወቅ፡፡

3) ክፍት የሆነ የህዝብ ቦታ ወይም ማጓጓዣ ባለንብረት ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ሰው ወይም የስራ ቦታን በተመለተ አሰሪ ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ሰው  በዚህ መመሪያ በተፈቀደው የተከለለ ቦታ ካልሆነ በስተቀር የሲጃራ መተርኮሻ ሳህን እንዲቀመጥ መፍቀድ የለበትም፡፡

4) ለህዝብ ክፍት የሆነ  ቦታ ወይም ማጓጓዣ ባለንብረት ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ሰው ወይም የስራ ቦታን በተመለከተ አሰሪ ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ማንኛውም ሰው በጉልህ የሚታይ ማጨስ በህግ የተከለከለ ነው የሚል ማሳሰቢያ ከነምልክቱ በአማርኛ እና/ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ወይም በአካባቢው የስራ ቋንቋ እና በአማርኛ መለጠፍ አለበት፡፡

17. ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ከትምባሆ ምርት ስለመጠበቅ

1) ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርትን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች ማቅረብ ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

2) የትምባሆ ምርት በሚሸጥበት ጊዜ ሻጩ የገዢውን ዕድሜ ከተጠራጠረ ህጋዊ ፓስፖርት፣ መንጃ ፈቃድ ወይም የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ በማየት ማረጋገጥ ይችላል፡፡

3) የትምባሆ ምርቶችን በድረ-ገጽ መሸጥን ጨምሮ የትንባሆ ምርትን ለመሸጥ ወይም እንዲሸጥ ለማድረግ ወይም ሽያጩን ለማቀላጠፍ ገዢ እና ሻጭ በአንድ ተመሳሳይ ቦታ ፊት ለፊት ሳይገናኙ የሚደረግ የትንባሆ መገበያ መንገድ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

18. ሲጋራን በነጠላ ስለ መሸጥ

1) የሲጋራ ምርትን በነጠላ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡
2) የትንባሆ ምርት የሚሸጠው እንደ አግባቡ የተወሰነውን የሲጃራ ወይም ትንባሆ ቁጥር ወይም ክብደት በያዘ ባልተከፈተ ፓኬት ወይም ማሸጊያ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት የጤና ማስጠንቀቂያ መያዝ ይኖርበታል፡፡
3) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ነጠላ” ማለት በሲጋራ ፓኬት ውስጥ ከሚገኙ ሲጋራዎች ውስጥ በቁጥር አንዷን የሚገልጽ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## አፈጻጸም

19. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1) በአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ አግባብ ባልሆኑ የትምባሆ ምርቶችና ሕጉን አክብረው ባልተገኙ ድርጅቶች ላይ ተላልፈው እንደተገኙበት የጥፋት ተግባር መጠን አስፈላጊ የሆኑ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወሰዳል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ስላስተሻሸግ፣ ገላጭ ጽሁፍ እና በመመሪያው የተቀመጡት ሌሎች ጉዳዮች ሳያከብሩና የትምባሆ ምርትን ለገበያ በሚያቀርቡ አምራቾች፣ አስመጪዎችን እና ጅምላ አከፋፋዮች ላይ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ፣ ልዩ ፈቃድ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ እና ሌላ አግባብ ያለውን ተጨማሪ እርምጃ በምርቱ ላይ ወይም በድርጅቱ ላይ ይወሰዳል፡፡

3) ባለሥልጣኑ አስቀድሞ የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃን በተመለከተ የሚያጠናክርለት ተጨማሪ ምክንያት ካገኘ የተጠቀሰውን ድርጊት ፈጽመው በተገኙ በአምራቾች፣ በአስመጪዎችና በጅምላ ሻያጮች እጅ የሚገኙትን ሕገ-ወጥ የትምባሆ ምርቶች ይያዛል፣ እንዲወገድ ያደርጋል፡፡

4) የትምባሆ ችርቻሮ ንግድንና ሌሎች በክልል ደረጃ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ጉዳዮችን በተመለከተ በክልል ደረጃ የሚገኝ አግባብ ያለው አካል እንደ አግባቡ ሕገ-ወጥ የትምባሆ ምርቶችን ሊይዝ ወይም ሊያስወግድ፣ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ፣ ልዩ ፈቃዱን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ወይም ሌላ አግባብ ያለው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## 20.በወንጀል ተጠያቂ ስለማድረግ

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆንበት ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ቢጥስና የህግ ጥሰቱ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ ሕግ፣ ስለምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁጥር 661/2002 ወይም በሌሎች የሕብረተሰብ ጤና ሕጐች የወንጀል ሀላፊነት የሚያስከትል ጥፋት ፈጽሞ ቢገኝ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 21. ህገ-ወጥ የትምባሆ ምርት ንግድ

1) ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርትን በህገ-ወጥ መንገድ ማስመጣት፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት፣ መሸጥ፣ መያዝ ወይም በማንኛውም ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ገበያ ውስጥ ማስገባት አይችልም፡፡

2) አግባብ ያላቸው የመንግስት አካላት ህገ-ወጥ የትምባሆ ንግድን ጨምሮ የትምባሆ ምርት ዝውውርን በሚመለከት መረጃ የመያዝ እና የመከታተል ግዴታ አለባቸው፡፡

3) በህገ-ወጥ መንገድ የተያዘ የትምባሆ ምርት እና ከህገ-ወጥ የትምባሆ ምርት ንግድ ጋር በተያያዘ የሚገኝን ትርፍ ወይም ማንኛውም ገቢ ተፈጻሚነት ባላው የሀገሪቱ ህግ መሰረት አግባብ ያለው የመንግስት አካል ይወረሳል፡፡
4) አግባብ ያለቸው የመንግስት አካላት ህገ-ወጥ የትንባሆ ንግድን ለመቆጣጠር አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለባቸው፡፡

22. የመተባበር ግዴታ

አግባብ ያላቸው አካላት በዚህ መመሪያ የተሰጠውቸን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና  የክልል መንግሥት አካላት እንዲሁም አግባብ ያላቸው የግል ተቋማት እና ግለሰቦች ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

23.ስለ ንግድ ሰንሰለት

የትምባሆ ምርት አምራቾችና አስመጪዎች የትምባሆ ምርትን የሚያቀርቡት አግባብ ካለው አካል የተሰጠ ህጋዊ ልዩ ፈቃድ ላላቸው ጅምላ አከፋፋዮች ብቻ ነው፡፡

24. ስለ ትምባሆ ምርት አወጋገድ

1) ህገ-ወጥ የሆኑ የትምባሆ ምርቶች፣ ማምረቻ መሳሪያዎችን እና ተያያዥ ምርቶች ሊወገዱ የሚችሉት የህብረተሰብ ጤናን በማይጎዳ ወይም አካባቢን በማይበክል መልኩ መሆን አለበት፡፡
2) የትምባሆ ምርት ማስወገድ የሚቻለው አግባብ ያለው አካል በማሳወቅ እና ተገቢውን መመሪያ ወይም ጋይድላይን መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

25.የአገልግሎት ክፍያ

በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎት የሚሰጠው ሰው አግባብ ባለው የመንግስት አካል በሚወስነው የክፍያ ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት።

## 26.ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ልምድ ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚት አይኖረውም፡፡

## 27.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1) የማሸጊያና ገላጭ ጽሁፍ ይዘትን እንዲሁም ስለ ትምባሆ ምርት ይዘት እና ለባለስልጣኑ ይፋ የሚደረግ መረጃን ጨምሮ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት ያሉ ድንጋጌዎች  ይህ መመሪያ ከጸደቀ ከስድስት ወር በኂላ ይጸናሉ፡፡
2) ከዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት በስተቀር ያሉ ሁሉም ድንጋጌዎችን መመሪያው ከጸደቀበት ቀን ከአንድ ወር በኂላ ይጸናሉ፡፡
3) ይህ መመሪያ መጋቢት 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ጸድቋል፡፡

**አቶ የሁሉ ደነቀው አላምነህ**

**ዋና ዳይሬክተርየኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን**